# ዜና ስለ ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት

ዜና ሰልፍ ሰፕላይ በየሁለት ወሩ አንዴ በ ሰልፍ ሰፕላይ ግብረ ሐይል በኢትዩጵያ አማካይነት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህም ግብረ ሐይል በመንግስት ተቋማትና ከልማት አጋሮች የተወጣጣ ሮረም ነው፡፡ የጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ዜና በማዘጋጀት ረገድ ቅድሚያው ወስዷል፡፡

*ፊለፊት ገፅ ቃለ ምልልስ*

- ◇ ፕሮጀክቱ ከወጣ በኃላ የባለገመድ ፓምፕ ስርጭትን በተመለከተ እኔ በጣም ተስፋ አደርጋለሁ!
- ◇ ከተርሚናል ኢቫሊዮሽን አባላት ጋር የተደረገቃለ ምልልስ

*መረጃ*

- ◇ የተከናወኑ እና ከመጪው ሰኔ እስከ መስከረም 2016 ለመተግበር በዕቅድ

*በአቻ አጋሮች እየተከናወነ ያሉ ስራዎች*

- ◇ የራስ አገዝ ውሃ ውሃ አቅርቦትን የማስተዋወቅ ስራ፡ በወረዳ ደረጃ በአተገባበር ዙሪያ የገጠሙ ችግሮች
- ◇ የባለ ገመድ ፓምፕ የተከላና ጥገና ስልጠና በከፋና ቤንች ማጂ ዞኖች

## “ ፕሮጀክቱ ስራውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ የባለ ገመድ ፓምፕ ስርጭትን በተመለከተ እኔ በጣም ተስፈኛ ነኝ ”
## የዋስ ሮፐስ ቡድን ከተርሚናል ኢቫሊዮሽን አባላት ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ!



አቶ አጋሽ (በስተቀኝ) እና አቶ በቀለ (በስተግራ) ከገምጋሚ ቡድን አባላት ጋር በታርጌት ወረዳዎች ያደረጉትን የግምገማ ውጤት ለካውንተር አጋሮች ሲያቀርቡ (ፎቶ ዋስ ሮፐስ)

አንድን ስራ ጀምሮ ለማጠናቀቅ ሁልጊዜም ቢሆን ወቅት አለ (በጊዜና በሰአት የተገደበ ነው)፡፡ በምህፃረ ቃል ዋስ ሮፕስ ብለን የምንጠራው ፕሮጀክት ስራውን አጠናቆ ከመውጣቱ በፊት ምን ያህል ስኬታማ እንደሆነ አጠቃላይ የሆነ ግምገማ ሲካሆድ ቆይቷል፡፡ እ.ኤ.አ ከሰኔ 13 እስከ ሐምሌ 1 2016 ድረስ ሶስት ጃፓናዊያን እና ሶስት ኢትዮጵያውያን አባላት ያሉበት ገምጋሚ ቡድን ስራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

የዋስ ሮፕስ ቡድን ስለነበረው ሂደት ከቡዱኑ አባላት መካከል ከአቶ አጋሽ አስማማው ከውሃ ፣ መስኖ እና ኤሌክትርክ ሚኒስትር አማካሪ እና አቶ በቀለ በለጠ በደቡብ ክልል ውሃ እና መስኖ ልማት ቢሮ ሶሾዎ ኢኮኖሚስት ጋር ቃለ ምልልስ አድርጓል፡፡“በአጠቃላይ ሂደቱ ግልፅና ሁሉንም በሚያግባባ መልኩ የተከናወነ ነው ፡፡በሪፖርታችን ያሰፈርነው ያመንበትን ነው፡፡ ይህንንም በግምገማ ውጤት ሪፓርታችን ላይ አካተነዋል፡፡በሂደቱም ብዙ አዎንታዊ የሆኑ ነገሮችን ለማየት ችለናል፡፡‶ ይላሉ አቶ አጋዥ ንግግራቸውን ሲቀጥሉ “ፕሮጀክቱን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ከቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት ጋር የፈጠረው ትስስር ነው፡፡የቴክኖሎጂ ሽግግሮችና ግባአቶች በሌሎች የመንግስት ተቋማት ላይ ጥገኛ ቢሆን ኖሮ ለዘለቄታው ሊያመጣ በሚችለው ለውጥ ላይ ጥርጣሬ ሊኖረኝ ይችል ይሆን ነበር፡፡ነገር ግን በዚህ ፕሮጀክት ያየነው ቴክኖሎጂው የተሸጋገረው ወደ ቴክኒክ እና ሙያ ተቋማት በመሄኑ የተጀመረው ስራ ወይም ሲስተም በራሱ ሊራመድ የሚችልበት መንገድ አለ፡፡በግምገማ ጊዜ ካስተዋልኩት የፕሮጀክቱ ጠንካራ ጎን አንዱ ይህ ነው ማለት ይቻላል፡፡”

አቶ አጋዥ ፕሮጀክቱ ስራውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ ስላለው ተስፋ አስተያየታቸውን ሲያክሉ “ለኛ ዋናው ጉዳይ ፕሮጀክቱ የጀመረውን መስመር አስፋፍቶና አጠናክሮ መስቀጠሉ ላይ ነው፡፡

ክልሉ ብዙ ኢንቬስትመንት ግብአቶች እና የሙያ ስልጠናዎችን ጨምሮ በርከት ያሉ ስራዎችን ተረክቦ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

ይህም ደግሞ ወጥነት ባለው መንገድ ሕብረተሰቡን በማሳተፍና ከባለድርሻ አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ ግንኙነቶችን በመፍጠር የሚከወን ይሆናል፡፡ እነዚህ ነገሮች በሚገባ ከተከናወኑ ፕሮጀክቱ ጊዜውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ የባለገመድ ፓምፕ ስርጭት ስራ እንደሚቀጣል እኔ በጣም ተስፈኛ ነኝ፡፡

የደቡብ ክልል ውሃ እና መስኖ ልማት ቢሮ ወደ ዞኖች እና ወረዳዎች የ10000 የባለገመድ ፓምፕ ስርጭት ከጀመረ ሁለት ዓመታት ያህል አልፏል፡፡ በአንዳንድ ዞኖችና ወረዳዎች የተከላው ሂደት እየተፋጠነ ይገኛል፡፡ አቶ በቀለ በለጠ የክልሉን ውሃ እና መስኖ ልማት ቢሮ በመወከል በግምገማ ሂደቱን የተሳታፉ ነበሩ፡፡

የተገኙ ልምዶችና ዕውቀቶችን በክልሉ የባለገመድ ፓምፕ ባልደረሰባቸው አከባቢዎች እንዴት ማስፋትና አጠናክሮ መሄድ ይቻላል የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱ “እንደ ክልል ላለፉት ሶስት ዓመታት በፕሮጀክቱ ሲያከናውኑ በቆዩት ሂደቶች ትምህርቶችን እና መልካም ልምዶችን ወስደናል”፡፡ ፕሮጀክቱ የተራመደባቸው እያንዳንዱ መንገድ ክልሉ ለሚያሰራጨው 10000 የባለገመድ ፓምፕ ተከላ ስርጭት በከፍተኛ ደረጃ ያግዛሉ ብዬ አምናለሁ፡፡” ይላሉ አቶ በቀለ አስተያየታቸውን ሲቀጥሉ “በባለድርሻ አካላት አከባቢ ጥሩ የሆነ በራስ መተማመን ተፈጥሯል ሲስተሞች በሚገባ ዳብረው በፕሮጀክቱ አማካይነት ተዘረግተዋል፡፡ እኔ እንደማምነው እነዚህ ጉዳዮች አጠቃላይ የስራው ዋና አንኳር ነጥብ ናቸው ብዬ እወስዳለሁ፡፡ ሆኖም ግን ይህ ማለት በግምገማ ሂደታችን ላይ ችግሮች አላስተዋልንም ማለት አይደለም፡፡

እኔ እንደማስበው እንደነዚህ ያሉ ክፍተቶችን ክልሉ ጣልቃ እየገባ መሙላት አለበት፡፡ እግረ መንገዱንም የተገኙ ትምህርቶችን ለሌሎች ዞኖች እና ወረዳዎች መውሰድ እና ማስፋፋት አለበት፡፡”

አቶ በቀለ ፕሮጀክቱ ስራውን አጠናቆ ከወጣ በኃላ ስላለው ተስፋ አስተያየታቸውን ሲያክሉ “ቅድም ለማለት እንደሞከርኩት ፕሮጀክቱ የገመድ ፓምፕ ስርጭት ስራን ለማስቀጠል የሚያስችል ጥሩ የሆነ ምቹ ሁኔታን ጥሎልን ነው የሚሄደው ፡፡ በመሆኑም ቀሪዎቹ በክልሉ የሚገኙትን የባለገመድ ፓምፖችን በአጭር ጊዜ ተክሎ ለማጠናቀቅ የሚያስችል መልካም ዕድል አለ፡፡ ብዙ ነገሮች መስመር ላይ ይገኛሉ፡፡ስለሆነም ክልሉ የተቀሩትን ፓምፖች ለማጠናቀቅ ይቸግረዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡አንዳንዴ በአባወራ ደረጃ የሚከናወኑ የራስ አገዝ ስራዎች ቀላል አይደሉም፡፡

# የገመድ ፓምፕ የተከላና ጥገና ስልጠና በከፋ እና ቤንች ማጂ ዞን

**JICA WAS-RoPSS**

በደቡብ ክልል ውሃ እና መስኖ ልማት ቢሮ በጃይካ ዋስ ሮፐስ ፕሮጀክት ድጋፍ ከሚያከናውናቸው ስራዎች አንዱ የሆነው እ.ኤ.አ ከሐምሌ 11 እስከ 23 2016 በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ለሁለት ሳምንታት የገመድ ፓምፕ ስልጠና እና ጥገና በከፋና ቤንች ማጂ ዞን ተካሄዷል፡፡ ስልጠናው ከአራት ወረዳዎች ለተመረጡ 23 ወንድና ለሶስት ሴት የአከባቢ ባለሙያዎች እንደሁም ለአራት የወረዳ ውሃ ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም በራስ ተነሳሺነት ከከፋ ዞን የመጡ ባለሙያም በስልጠናው ላይ ተካፋይ ነበሩ፡፡ ሁሉም ስልጣኞች ማለት በሚቻል ደረጃ በፍላጎትና በተነሳሽነት የገመድ ፓምፕ ተከላ ስልጠናውን ተከታትለዋል እንዲሁም ለቀጣይ ስራ ራሳቸውን ብቁ የሚያደርጋቸውን ክህሎት አግኝተዋል፡፡

በከፋ ዞን 79 በቤንች ማጂ 100 ለሚጠጉ የገመድ ፓምፖዎች የተሰራጩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 7 በከፋ ዞን እና 6 በቤንች ማጂ ስልጠናውን ምክንያት በማድረግ ተተክለዋል፡፡

የስልጠናው አንዱ አካል የነበረው የገመድ ፓምፕ አጠቃቀምና ጥገና ዙሪያ ለስልጣኞች በተጓዳኝ የተሰጠ ሲሆን ሰልጣኞቹም የተቀበሉትን ትምህርት ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ችለዋል፡፡ በሌላ መልኩ በፕሮጀክቱ አባላት ከፍተኛ ደስታን የፈጠረው ደግሞ ተጠቃሚዎች የፓምፕ ተከላ እንደተካሄደ በፓምፑ አካባቢን በማጠር ሳር የማልበስና በአበባ የማሳመር ስራ መጀመራቸው ነው፡፡የጊንቦ ወረዳ የውሃ እና ማዕድን ቢሮ ምክትል ሐላፊ የሆኑት ወ/ሮ ሀብታም ስለስልጠናው በሰጡት አስተያየት ሰዎች እንዲህ ዓይነት ቴክኖሎጂ እንደሚያስፈልጋቸውና ተከላው እንደሚያስቀጥሉ ተናግሯል፡፡ ሌሎችም በገጠር የሚኖሩ ነዋሪዎች በቤታቸው አቅራቢያ ቴክኖሎጂው እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል፡፡ ወ/ሮ ሐብታም ሐሳባቸውን ሲቀጥሉ ወደ ፊት መጓዛችንን እናቆምም "በማለት ስራውን ለማስቀጠል ቁርጠኝነታቸውን በከፍተኛ ስሜት ገልፀዋል፡፡ የስልጠናው ተሳታፊዎች ያገኙትን ዕውቀት በብቃት ለማረጋገጥ በሳምንት ጊዜ ውስጥ በሐዋሳ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና የሚወሰዱ ይሆናል፡፡



በከፊል በሼ ቤንች ወረዳ በቤንች ማጂ ዞን በስልጠና ላይ የጉድጓድ ማጥበቢያ እየደረደሩ ፎቶ፡ ዋስ - ሮፕስ

# በባለገመድ ፓምፕ አጠቃቀም እና ጥገና ዙሪያ በከፋ ዞን መልካም ተሞክሮ

አቶ ሲሳይ በከፋ ዞን በጊንቦ ወረዳ በኩጥ ቀበሌ ነዋሪና በቅርቡ የባለገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ የሆኑ አርሶ አደር ናቸው፡፡በቅርቡ ባገኙትም የገመድ ፓምፕ አማካይነት ኑሮአቸውን ለማሻሻል ቁረጠኝነታቸውን ገልፀዋል፡፡



የአቶ ሲሳይ ፓምፕ የተተከለበት ቦታ የቡና ችግኝ ያለበት ነው፡፡የከፋ ተጠቃሚዎች የገመፓምፓቸውን እንደተተከለ ወዲያው አጥረውታል (ፎቶ በዋስሮፕስ)

አቶ ሲሳይ ፓምፑን መጠቀም ሲጀምሩት ገና ጥቂት ቀናት ቢሆንም ፓምፑ የተተከለበት ቦታ የቡና ችግኝ/እርሻ ያለበት በመሆኑ ለተለያዩ አገልግሎቶች ከፓምፑ የሚገኘውን ውሃ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ከፕሮጀክቱ ለመጡ ኀቢኚዎች ገልፀውላቸዋል፡፡ የፓምፑን አከባቢ በአጥር ያጠሩና በአበቦች ያስጌጡት ሲሆን ውሃውን ለተለያዩ የቡና ችግኞችን ለማፍላት እና ለፖም እና ሌሎች የፍራፍሬ ተክሎችን ማበልፀግ መጀመራቸውን ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ሲሳይ ገለፃ የገመድ ፓምፕ ተጠቃሚ ለመሆን ፍላጎት ያደረባቸው ስለ ገመድ ፓምፕ ቴክኖሎጂ በተለያዩ ስብሰባዎች በተደረጋላቸው ገለፃ ነው፡፡ ቴክኖሎጂውም የቤተሰቦቻቸውን ሕይወት በብዙ መልክ ሊለውጥ እንደሚችል ያስባሉ፡፡ ደህንነቱን የተጠበቀ የመጠጥ ውሃ፣ ለቤት ውስጥ ፍጆታ፣ ልጆቻቸውና እንስሶቻቸውን ለማጠጣት እንደሚያውሉት ይገልፃሉ በሌላ መልኩ ደግሞ እንስሶች በጉድጓድ ውስጥ እንደይወድቁ ፣ የሞቱ ድመቶች እና አይጦች የጉድጓድ ውሃውን እንዳይበክሉ ያደርጋል፡፡

አቶ ሲሳይ አሁን ያገኙትን የባለገመድ ፓመፕ ለመጠጥና ለቤት ውስጥ አገልግሎት ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ገልፀው በተጨማሪ ችግኞችን ለማፍላት እንደሚጠቀሙባቸው ገልፀዋል፡፡

# የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦትን ማስተዋወቅ፡ በወረዳ ደረጃ አተገባበሩ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች

**IRC, Millennium Water Alliance**

ያልተሻሻለ የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ወይም ያልተሸፈነ የጉድጓድ ውሃ አቅርቦት እና የምንጭ ውሃዎች ለመጠጥ ከሚውሉ የውሃ አቅርቦቶች ዋናዎቹና 28 ሚሊዮን የሚጠጋ በገጠር የሚኖረው ሕዝብ የነዚህ የውሃ ምንጮች ጥገኛ እንደሆነ እ.አ.አ 2015 የወጣ መረጃ ያሳያል፡፡ ምንም ያህል ኢንቨስትመንት ፈሰስ ቢኖርም የውሃ አቅርቦቶች ቢስፋፉም እድገቱ እ.አ.አ 1990 ጀምሮ ለውጥ አላሳየም የዚህ አንዱ ምክንያት በሁለት ዲጂት እያደገ ያለው የገጠሩ ሕዝብ ቁጥር መጨመር ሊሆን እንደሚችል ይታመናል/(ጄ ኤም ቲ ዳታ) የዩኒቨርሳል አክሰስ ፕላን በ2030 ያለ ራስ አገዝ ተጓዳኝ ስራ ዕውን የሚሆን አይመስልም፡፡የሚሊንየም ዋተር አሊያንስ  እና አጋሮቹ የሶስት ዓመት ከኮናርድ ሐልተን ፋውንዴሽን ግራንት በዋሽ በኩል እየተካሄደ ያለው የራስ አገዝ ውሃ አቅርቦትን ማፋጠንን እንደ አንድ ኮምፓነንት እየተገበረ ይገኛል፡፡እ.ኤ.አ በሴኔ 23 2016 ከመንግስት አካላት ከኬር ኢንተርናሽናል በጋራ በደቡብ ጎንደር በራስ አገዝ ዙሪያ በቅንጅት ስልጠና እና የክለሳ ስብሰባ ተደርጎ ነበር፡፡ በስልጠናው ላይ የተነሱት ሐሳቦች በብሔራዊው የራስ አገዝ አክስለሬሽን ፓሊሲ አተገባበር ዙሪያ አይን ገላጭ ነበር ማለት ይቻላል፡፡የራስ አገዝ በዋሽ ሴክተር ዕቅድና ሪፓርት ውስጥ ማካተት የኢትዮጵያ መንግስት ራስ አገዝ እንደ አንድ ሰርቪስ ሞዳሊቲ መጠቀም ከጀመረ ሶስት ዓመታት አልፈዋል፡፡ የተለያዩ ለራስ አገዝ ስትራቴጂን የሚረዱ ሀሳቦች የተቀረጸ ቢሆንም አሁንም ድረስ ራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት በውሃ ሴክተር ማዕቀፍ ውስጥ በብሔራዊ፣ በክልል እንዲሁም በዞኖችና ወረዳዎች ዕቅድ ውስጥ አልተካተተም፡፡ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ በፓይለት ደረጃ እየተገበራቸው ካሉት ጥረቶች አንዱ ወረዳዎች በስራቸው የሚገኘውን  የዋሽ ሰንሰለት ውስጥ ራስ አገዝ አክስለሬሽን ፕሮግራምን እንዲያዳብሩ መረዳት ነው፡፡ሁሉም ወረዳዎች በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ/ ፕሮጀክት ድጋፍ የሚደረግላቸው የራስ አገዝ ዕቅድን በወረዳው ከሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/ NGOs ጋር በመሆን እና ከሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤ/ቶች በቅንጅት የቅድመ ጥናት መነሾ እንዲቀርፁ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን የተወጠኑ ዕቅዶች በወረዳዎቹ የመንግስት አካላት ዕቅድ ለራስ አገዝ ክንውኖች ታሳቢ እንዲሆኑ በመወሰኑ በዛ መልኩ ዕቅድ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡ሆኖም ግን ለአተገባበሩ ሂደት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ ሂደቱ አዝጋሚ ነበር፡፡ ራስ አገዝ ብዙ ጊዜ ከላይኛው መዋቅር እስከ ወረዳ ደረጃ ባለው ሂደት ውስጥ በአንድ ዕቅድ አይካተትም፡፡ በዕቅድ ደረጃ ብቻ ሳይሆን የራስ አገዝ የሪፖርት ስራዎችም ክንውኖችም ቢሆኑ በወረዳው ደረጃ እንዲያቀርቡ አይገደዱም፡፡ሆኖም ግን አንዳንዴ ክልሎች “የቡድን የራስ አገዝ” አንቅስቃሴዎችን በየሴክተሩ ስብሰባዎች ላይ ያቀርቧቸዋል፡፡ አንዳንድ የየወረዳዎች የራስ አገዝ እንቅስቃሴዎች ለስራው ዕምቅ አቅም ባለባቸው ቀበሌዎች ውስጥ በዕቅድና በረፓርት ፎርማት ውስጥ ካለተካተቱ በቀር በየወረዳዎቹ አሁንም ቢሆን ራስ አገዝ በቂ ትኩረት አያገኝም፡፡



ራስ አገዝ ዎርክሻ ደቡብ ጎንደር(Photo by IRC)

## ራስ አገዝ በሚገባ ሲሰራበት

የሚሊንየም ዋተር አሊያንስ የራስ አገዝ ፕሮጀክት ለ55,000 ሰዎች የንፁህ ውሃ አማራጭን ለግል እና ለቡድን የራስ አገዝ ተቋማት ግንባታ ትኩረት አድርጎ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ሰባት ወረዳዎች ዕቅዱ ሊተገበር ይችላል ይህም በከፍተኛ ደረጃ በግል ያሉ ጉድጓዶች በአባወራዎች ደረጃ መከፋፈል ስላለ በዕቅድ ሊደረስበት የታቀደውን የአባወራ ቁጥር ለመድረስ ያስችላል፡፡ የውሃ ግንባታዎች በርግጥም በተጠቃሚዎች በጋራ መከፋፈልና መጠቀም አለበት፡፡አንዳንዴም በግለሰብ ይዞታ ያሉ የጉድጓድ ውሃዎችም ጭምር በርከት ላሉ አባወራዎች ሲከፋፈል ይታያል፡፡ በእጅ የተቆፈሩ ጉድጓዶች በመርህ ደረጃ በሚገባ እንዲሸፈኑና ደህንነቱ የተረጋገጠ የውሃ አቅርቦት ሽፋን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ምንም እንኳን አሁን ያለው የሞኒተሪንግ ሲስተም በምንም አይነት መልኩ በአባወራ ደረጃ የሚካሄድን የራስ አገዝ ሂደትን ለመጠቀም ሆነ ለማስቀጠል እድል የሚሰጥ አይደለም፡፡

በርግጥም አጠቃላይ የራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት ለመገምገምና ለመቆጣጠር መሞከር አዳዲስ ሰዎች ወደ ንፁህ ውሃ አቅርቦት ሂደት ከማምጣት ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡የውሃ ምንጭ በመኖሪያ ቤት አከባቢ አለ ማለት ቡዙ ውሃን ለከብቶች ለአነስተኛ መስኖ ፣ ለግልና ለአከባቢ ንፅህና እንዲሁም ለተለያዩ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶችን ለማፍራት እንዲሁም የገቢ መጠን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ይህም ውሃን ለመሰብሰብ የሚባክነውን ጊዜ ይቆጥባል፡፡ በተጨማሪም ድህንነቱ የተረጋተጠ የውሃ ምንጭ ለመጠቀም ያስችላል ማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ አዎንታዊ ግብአቶችን አካቶ በሞኒተሪንግ ስርዓት ውስጥ ማካተት ተደራሽነትን ከንፅህ ውሃ አቅርቦት አንፃር ሊያሳየን ይችላል፡፡

## የብድር አገልግሎት ለራስ አገዝ ውሃ አቅርቦት



የቡድን ውይይት ሸሸድር ዙሪያ

ለራስ አገዝ የውሃ አቅርቦት እንዲረዳ ታስቦ አይ አር ሲ (IRC) ከሚሊንየም ዋተር አሊያንስ ጋር በመሆን በ7 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኝ አባወራዎች ባደረጉት ጥናት አባወራዎቹ መጀመሪያ ላይ ለሚኖሩ የጉድጓድ ቁፋሮ እና ግንባታ ብቻ ገንዘባቸውን የሚያወጡ ሲሆን ሆኖም ግን አባወራዎቹ የራሳቸውን ጉድጓድ ከፍ ወዳለ ደረጃ መገንባት ቢፈልጉ የብድር አገልግሎት ውሃን ለመሳብ የሚያስፈልጉ ፓምፕ ግዥዎች ያስፈልጓቸዋል፡፡የሚሊንየም ዋተር አልያንስ አጋር አንዱ የሆነው "ዋተር ዶት ኦርግ" /water.org/ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በአባወራ ደረጃ ለሚካሄዱ የራስ አገዝ እንቅስቃሴዎች እንዲያበድሩ ከፍተኛ ጥረት ሲያደር ቆይቷል፡፡በዚህም መነሻነት የተለያዩ ድጋፎችን እና ስልጠናዎች ሲያከናውን ቆይቶ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጋር የመግባቢያ ሰነድ ፈርመዋል፡፡ በቅርቡ የተቋሙ ተወካዮች በተገኙበት በተካሄደው ስብሰባ ከወረዳዎቹ ውስጥ አንደኛው በዋሽ በኩል ብድሩ እንዲመቻች መመሪያ የተቀበሉ መሆኑን የወረዳው ተወካይ ገልጸዋል፡፡

አሁን ጥንቃቄ በተሞላበት ሂደት የብድር አገልግሎት መሰጠት መጀመሩን ገልፀዋል፡፡ ብድሩም እየተሰጠ ያለው አባወራዎቹ በጋራ ለራስ አገዝ አገልግሎቶች እንደሚያውሉ ከታወቀ ብቻ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ ለጓሮ መስኖ ፣ለአበባ እርሻ ወይም ግብርና ምርቶች አገልግሎት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ አበረታች እና የራስ አገዝ አክስለሬሽን ጥረትን እንደሚያግዝ ይታመናል፡፡

## ለወደፊቱ

በሀገር ደረጃ በውሃ መስኖ እና ኤሌክትሪክ እየተመራ የሚካሄድ የሰልፍ ሰፐላይ ግብረሐይል (ከልማት አጋሮች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) የተወጣጣው ቡድን ስራዎቻቸው ቀንሰዋል፡፡ ራስ አገዝ በዋሽ ዕቅድ እና ሪፓርት ሂደት ውስጥ ለማካተት ከፍተኛ የሆነ ጥረት እና ቅስቀሳ በማድረግ ላይ ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም ግብረሐይሉ ሂደቱን የሚዳስስበትን ሲስተም እንደሚዘረጋ ለማድረግ የተለያዩ ቅስቀሳዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህንንም ማድረግ የተጠቃሚ ቁጥር ለማብዛት ብቻ ሳይሆን የራስ አገዝ የውሃ ግንባታ ዙሪያ የተገኙ ጥቅሞችን ለማዳረስ እና አገልግሎት ሰጪውንም በስራው ዙሪያ ለመገምገም ይረዳል፡፡

## እ. ኤ. አ ለሰኔ እና ሐምሌ 2016 የተከናወኑ ስራዎች

ሰኔ 12 የዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት የግምገማ ጥናት እና የጣምራ ኮምቴ ስብሰባ

ሐምሌ የባለ ገመድ ፓምፕ ተከላ አጠቃቀምና ጥገና ስልጠና በቤንች ማጅና ከፋ ዞን /ጃይካ ዋስ ሮፕስ ፕሮጀክት/

- በወረዳ ደረጃ የማነቃቂያ ስልጠና በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ የራስ አገዝ ፕሮጀክት ወረዳዎች
- የራስ ፈጠራ ስልጠና ለግሉ የስራ ፈጣሪዎች በሚሊንየም ዋተር አሊያንስ ወረዳዎች
- ውይይቶችና ስብሰባዎች ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ጋር (በሚሊንየም)
- ከደቡብ ጎንደር ኬር ቢሮ አባላት ከአማራ ብድርና ቁጠባ አባላት ከደቡብ ጎንደር ዞን እና ከዳራ፡ ፋረታ እና እስቴ ወረዳዎች ዋና ዋና ቁልፍ ተሳታፊዎች የአንድ ቀን ስብሰባ በአማራ ብድር (በሚሊንየም)
- የግሉን የቢዚነስ አመልካቾች ለቻሌንጅ ፈንድ ድጋፍ ማድረግ (በሚሊንየም)
- "የሚሊንየም ዋተር አሊያንስ " መደበኛ የሲቲረንግ ኮሚቴ ስብሰባ ስለተደረገባቸው ጉዳዮች እና የድርጊቱ መረሀ ግብር (በሚሊንየም)
- የማስታወቂያ ግብዓቶች አዘገጃጀት ፍላጎት ለመፍጠር (በሚሊንየም)
- ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ /ከአይ አር ሲ በጋራ የሚያመቻቹት የአለም አቀፍ ባክስቶፕ የድጋፍ ቡድን ወረሃዊ ጥሪ ለኢትዮጵያ (በሚሊንየም)
- የራስ አገዝ ግብረ ሐይል ስብሰባ

## እ.ኤ.አ በነሐሴ እና መስከረም የሚሰሩ ስራዎች

ሐምሌ 30 - የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ለባለገመድ ፓምፕ ተካዮች (ጃይካ ዋስ ሮፕስ

በነሐሴ - በባለ ገመድ ፓምፕ የጥራት ቁጥጥር እና አሰራርና ጥገና ላይ የሚካሄድ ዋርክ ሾፕ (ጃይካ ዋስ- ሮፕስ)

- የራስ አገዝ ግብረ ሐይል ስብሰባ
- የቻሌንጅ ፈንድ አመልካቾችን መገምገምና መሸለም
- በቀበሌ ደረጃ ለአስተዳደር ለጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች ለልማት ሰራተኞች የሚሰጥ ስልጠና የሚሊንየም ዋተር አሊያንስ በሚሰራቸው ወረዳዎች
- የራስ አገዝ አክስሌሬሽን የማስተዋወቅ ስብሰባ በማህበረሰብ ደረጃ (ጉብኝት፣ የማነቃቂያ ሁኔታዎችን ማመቻቸት)
- ለግሉ የቢዝነስ ሴክተር አባላት የሚደረግ ድጋፍ እና የቴክኒካል ሲኪል ድጋፍ በስልጠና እና በኮችንግ
- የሚሊንየም ዋተር አሊያንስ አክስለሬሽን ፕሮጀክት የሲቲሪንግ ኮሚቴ የጋራ ስብሰባ እና የመስክ ጉብኝት
- አንዱን የራስ አገዝ ቴክኖሎጂ የቤት ውስጥ የውሃ ሕክምና ላይ በ "በመሞከር ይግዙ" የሚለውን አቀራረብ ማሳየት
- ሚሊንየም ዋተር አሊያንስ /ከአይ አር ሲ አለምአቀፍን የኋላ ደጀንነት ድጋፍ ወርሃዊ ጥሪ ለኢትዮጵያ —- ያመቻቻል
- ትምህርታዊ ጉዞ እና ሐሳብ የመለዋወጥ ፎረም እ.ኤ.አ በነሐሴ መጨረሻ /በመስከረም 2016 መጀመሪያ ላይ ይዘጋጃል

If you have any comments, questions, suggestions, please contact us at;

**JICA WAS-RoPSS Project**

Room # 012, Ministry of Water, Irrigation and Energy
Tel: +251 - (0)11-651-1455
Mob: +251 - (0)935-353210/12/14
E-mail : jica.ropepump.ethiopia@gmail.com

**Websites**

JICA http://www.jica.go.jp/oda/project/1100485/index.html (Japanese)
http://www.jica.go.jp/project/english/ethiopia/004/index.html (English)

MoWIE http://www.mowr.gov.et/
CoWASH http://www.cmpethiopia.org/
IRC http://www.ircwash.org/
A4A http://www.aquaforall.org/
RWSN http://www.rural-water-supply.net/en/resources/details/662
IRC http://www.ircwash.org/